Free digital copy from ServeNow

# ክርስቲያን ስለ መሆን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

ላርስ ዴንበርግ

ServeNow

Free digital copy from ServeNow

*ክርስቲያን ስለ መሆን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች*

*The Basic Things You Need to Know About Being A Christian* (Amharic)

ጸሓፊ፡ ላርስ ዴንበርግ

የቅጅ መብት © 2017 ሰርቭ ናው
በፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ፤ መብቱ የተጠበቀ

ISBN፡ 978-1-958730-63-8

የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጥኛ ጽሑፍ ጋር፤ በቢብሊካ የታተመ ©1993፤2003

The Bible in Amharic©United Bible Societies 1962
Holy Bible, New Amharic Standard Version (አዲሱ መደበኛ ትርጉም). Copyright © 2001 by Biblica, Inc.® በፈቃድ የተወሰደ: መብቱ በዓለም ዙሪያ የተጠበቀ ነው።

በሰርቭ ናው (*ServeNow*) የታተመ፣
1817 Austin Bluffs Parkway #110
Colorado Springs, CO. 80918, USA

Free digital copy from ServeNow

# ክርስቲያን ስለ መሆን ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች

## ክርስቲያን ምንድን ነው?

ረዘም ላሉት ዓመታት ወደ 100 አብያተ ክርስቲያናትን የመጎብኘት ዕድል አግኝቼ ነበር። እስከዛሬ ድረስ ባገኘኋቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ክርስቲያን መሆን ምን እንደሆነ በተደጋጋሚ እጠይቃለሁ። ከነዚሁ ሰዎች በሚሰነዘሩት የተለያዩ ምላሾች ውስጥ ውስን እውነት ብቻ ሲገኝ አብዛኛው እውነት ግን የተሸፈነ ነው።

እስቲ ከሰማኋቸው ምላሾች ጥቂቶቹን ላጋራችሁ። በመቀጠልም በእውነታው ፍለጋ ላይ በጋራ እንሰማራለን።

*ክርስቲያን ምንድን ነው? አንድ በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው ይመስለኛል።*

በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሕዝቦች በሆነ አምላክ ያምናሉ። ለምሳሌ በሕንድ አገር የሚኖሩ ሰዎች በብዙ አማልክት ቢያምኑም ያ እምነታቸው ክርስቲያን አያደርጋቸውም።

*ክርስቲያን ምንድን ነው? የሚጸልይ ሰው ይመስለኛል።*

እስላሞችም ይጸልያሉ። የሕንዱም ሆነ የቡዳሃ እምነት ተከታዮችም ይጸልያሉ። እንዲሁ ደግሞ ክርስቲያኖች ይጸልያሉ። ሆኖም ግን መጸለይ አንድን ሰው ክርስቲያን አያደርገውም።

*ክርስቲያን ምንድን ነው? ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ሰው ይመስለኛል።*

አንዳንዶች ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን በልማድ ወይም በቤተሰብ አባላት ግፊት ያደርጉታል። ሌሎች ደግሞ ስለ

Free digital copy from ServeNow

አንዳች ነገር ከመዳዳታቸው የተነሣ ይሄዳሉ። አንድ ወቅት ላይ የሆኑ ሌቦች ገንዘብ ለመስረቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ አሉ። ለዚህም ተግባር ወደ ቤተ ክርስቲያን ማቅናታቸው ክርስቲያን አላደረጋቸውም።

*ክርስቲያን ምንድን ነው? ከሌሎች ሰዎች የተሻለ ኑሮ የሚኖር ይመስለኛል።*

ብዙ ሰዎች ከነፍሰ ገዳዮች አንጻር የተሻለ ነገር እንዳላቸው ያምናሉ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ከቤተሰብ አባሎቻቸው አንጻር ራሳቸውን ሲመለከቱ በተወሰነ መልኩ የተሻልን ነን ብለው ያስባሉ። ነገር ግን በጉብዝና ክርስቲያን ከመሆን ይልቅ የሻይ ማንኪያን መቆፈሪያ አድርጎ በትልቅ ተራራ ውስጥ መሿለኪያ መቆፈር ይቀላል!

*ክርስቲያን ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ሰው ይመስለኛል።*

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚወዱ በየዕለቱ ያነቡታል። የኢአማኒያን አባት የሆነው ካርል ማርክስ ገና በአሥራ አምስት ዓመቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በአንደኛው ላይ ማብራሪያ ጽፏል። መጽሐፍ ቅዱስን ስላነበበ ብቻ አንድም ቀን ክርስቲያን ነኝ ብሎ ተናግሮ አያውቅም። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ለብዙ ሰዎች እጅግ ጠቃሚ ነገር ቢሆንም ማንበባቸው ከቶውኑ ክርስቲያን አያደርጋቸውም።

ክርስቲያን ምንድን ነው? ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚፈጽም ሰው ይመስለኛል። የቀድመችው ቤተ ክርስቲያን ሐዋሪያ የነበረው ጳውሎስ የግሪኳን አቴንስ ከተማ ሲጎበኝ አንድ አስደናቂ ነገር ተመለከተ። የአቴና ሰዎች ብዙ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን እንደሚፈጽሙም አየ። ይህንን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ 17:16-23 ላይ ማንበብ ትችላላችሁ።

*ጳውሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ፥ በከተማው ጣዖት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨበት። ስለዚህም*

Free digital copy from ServeNow

*በምኲራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር።*

*ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ። አንዳንዶቹም፦ “ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል?” አሉ፤ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሣኤውን ወንጌል ስለ ሰበከላቸው፦ “አዲሶችን አማልክት የሚያወራ ይመስላል፡” አሉ።*

*ይዘውም፦ “ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናል? በጆሮአችን እንግዳ ነገር ታሰማናለህና፤ እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንፈቅዳለን፡” ብለው አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ ወሰዱት። የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና።*

*ጳውሎስም በአርዮስፋጎስ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፦ “የአቴና ሰዎች ሆይ፥ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ። የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ፦ ‘ለማይታወቅ አምላክ፡’ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና። እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ።*

የአቴና ሰዎች ለማይታወቅ አምላክ መሥዋእት ያቀርቡ ነበር። የታወቁ ሃይማኖተኞች ነበሩ። ሆኖም ግን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን መፈጸማቸው ፈጽሞ ክርስቲያን አላደረገቸውም።

*ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።*

*ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች*

Free digital copy from ServeNow

*ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ፡- ‘እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና፡’ ብለው እንደ ተናገሩ፥ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን* (የሐዋርያት *ሥራ* 17:24-28)።

ሌሎች በፈቃዳቸው ወደ እግዚአብሔር ይሳባሉ። እግዚአብሔርን ለማየት እና ለመስማት ይሻሉ። ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ፍላጎት ካለህ ከዛሬ 2,000 ዓመታት በፊት የኖረ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስለሚባል ሰው ማወቅ ይጠበቅብሃል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሰዎች የርሱ ደቀ መዛሙርት እና ተከታዮች ነበሩ። ከርሱ *ጋራ* ነበሩ፣ አድምጠውታል፣ ከርሱ ተምረዋል፣ *ሥራ*ዎቹን ተመልክተዋል ደግሞም አግዘውታል። አሁንም አልተለወጠም። ስለ ኢየሱስ በምታነብበት ጊዜ ወደ ርሱ ደግሞ ጸልይ፣ ኢየሱስን አምልክ፣ ስለ ኢየሱስ አውራ፣ ይህም ቀለል ያለ እና የተለመደ የየዕለት ተግባር ይሆንልሃል። ኢየሱስን መከተል ባለ ምጡቅ አእምሮ ከመሆን ወይም ከሌሎች ሰዎች በተሻለ ግብረ ገብ ከመሆን *ጋር* በምንም አይገናኝም። ኢየሱስ ሲናገር *እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም*(ማርቆስ 10:15)። ኢየሱስ ክርስቶስን ፈጽመህ ስትታመነው የበለጠ እያወቅኸው ትሄዳለህ። የሆነ የማይታወቅ አምላክን ሳይሆን እራሱን እያመለክኽ ትረዳለህ። አዲስ ፍጥረት ነኽ። ይህም ማለት *ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል* (2 ቆሮንቶስ 5:17)።

በኢየሱስ የምድር ላይ ቆይታ ማብቂያ አካባቢ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የነበረው ፊሊጶስ *“ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል፡” አለው። ኢየሱስም አለው፡- “አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል* (ዮሐንስ14:8-9)። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ስላዩ እግዚአብሔር አብንም አይተዋል። እግዚአብሔርን

Free digital copy from ServeNow

ሊታይ ወይም ሊታውቅ ከወደድኽ፣ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ሊታውቅ ግድ ይላል። ይህም ክርስቲያን ለመሆን የመጀመሪያው ርምጃ ነው።

## *የሰው ልጅ አጣብቂኝ*

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መፍትሔ ያገኘ የሰው ልጅን አጣብቂኝ ውስጥ ያስገባ ሁኔታ አለ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሰው ልጆች የተጠቀሰው በመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ሲሆን *እግዚአብሔርም አለ፦ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።"*

*እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው* (ዘፍጥረት 1:26-27)።

ሰዎች እግዚአብሔርን አልፈጠሩትም። እግዚአብሔር ያንተ ፈጣሪ ነው። የእግዚአብሔር ምሳሌ ልትሆን ተፈጥረሃል። ነግር ግን የሆነ ነገር በመካከል ተፈጠረ። ገና ከጅምሩ ሁለቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ፤ እግዚአብሔር ለእነርሱ ከነበረው አሳብም እራሳቸውን አወጡ። በተጨማሪም በፍጥረት ታሪክ ውስጥ (ዘፍጥረት 2) እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰው ለአዳም መልካሙንና ክፋውን የምትለየዋን ዛፍ እንዳይበላ ትእዛዝ እንደ ሰጠው እናነባለን። ከዚያ ዛፍ  ፍሬ እንዲበላ አልተፈቀደለትም። በዘፍጥረት 3 ላይ አዳም እና የመጀመሪያዋ ሴት ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፈው ከዛፉ ፍሬን ቆርጠው እንደበሉ እንመለከታለን። አለመታዘዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ኀጢአት ይባላል። ከመጀመሪያው ኀጢአት የተነሣ አዳም እና ሔዋን ኀፍረት እና ፍርሃት ተሰማቸው። ይህንን አጣብቂኝ ጳውሎስ በሮሜ ለሚገኙ ቅዱሳን ሲጽፍ፦

Free digital copy from ServeNow

*ስለዚህ ምክንያት ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኀጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ* (ሮሜ 5:12)። ለዚህ አጣብቂኝ ኢየሱስ መፍትሔ ነው። የኢየሱስ ሕይወት ለምን ወሳኝ እንደሆነ ማንበብህን እንደቀጠልክ ትደርስበታለህ!

## *የክርስትና እምነት መሠረታዊ ጉዳይ*

የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት አካባቢ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ማበብ እንደጀመረች ብዙዎች የክርስትና እምነት እንዴት ያሉ እውነታዎች ሊኖሩት እንደሚችል ያስቡ ነበር። የነዚህንም ሰዎች መሠረታዊ እምነት ወንጌል ወይም የምሥራች ብለው ይጠሩታል። ስለዚህ፣ ጳውሎስ፣ ራሱ ከኢየሱስ ጋር በአስደናቂ መልኩ የተገናኘው ሰው፣ ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ለአንዱ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

*ወንድሞች ሆይ፥ የሰበክሁላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፤ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር፥ ብታስቡት፥ በምን ቃል እንደ ሰበክሁላችሁ አሳስባችኋለሁ።*

*እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን፡ ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፡- "መጽሐፍ እንደሚል፡ ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል፡ በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥*(1 ቆሮንቶስ 15:1-4)።

ኢየሱስ ስለ ኀጢአታችን ስለ ሞተ እና ከሙታንም መካከል ስለ ተነሣ፣ ከዚህ አጣብቂኝ እንዲታደገን ራሱን ኢየሱስን መጠየቅ እንችላለን። ያም የምሥራች ይባላል።

## ኢየሱስ ክርስቶስ ከአዲስ ልደት ጋር ያስተዋውቅሃል።

ስለ የምሥራቹ ለመግለጽ እና "ዳግም ልደት" ምን እንደሆነ ለማስረዳት መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን በምሽት ወደ ኢየሱስ

Free digital copy from ServeNow

ሄዶ እንዲያ ያለ ነገር መኖሩን ስለጠየቀው የኒቆዲሞስ ታሪክ እንመልከት።

*ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፡- "መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና፡ መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን፡" አለው።*

*ኢየሱስም መለሰ፡- "እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም፡" አለው።*

*ኒቆዲሞስም፡- "ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?" አለው።*

*ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- "እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።*

*'ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል' ስላልሁህ አታድንቅ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።"*

*ኒቆዲሞስ መለሰ፡- "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" አለው።*

*ኢየሱስም መለሰ እንዲህ አለው፡- "አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፥ ምስክራችንንም አትቀበሉትም።*

*ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?*

Free digital copy from ServeNow

*ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።*

*ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና* (ዮሐንስ 3:1-17)።

ኒቆዲሞስ መልካም፣ ሃይማኖተኛ እና የተከበረ ሰው ነበር። ምናልባትም የሸንጎ አባል ነበር። ነገር ግን ከምንም በላይ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ፈለገ።

ለኒቆዲሞስ አዲስ የልደት ቀን አስፈልጎታል! ዳግም መወለድ እንዳለበት ተረዳ። ልክ እንደ እኔ እና እንዳንተ ከወላጆቹ በአካል አንድ ጊዜ ተወልዷል። ሆኖም ግን ኒቆዲሞስ መንፈሳዊ ውልደት አስፈላጊው ነው። ሁኔታው አወዛጋቢ ቢመስልም ኢየሱስ እንዴት ሊሆን እንደሚችል አብራርቷል።

*አንዱ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር እንዲህ ጽፏል፦ ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው* (ዮሐንስ 3:12-13) ።

**ክርስቲያን ምንድነው?** ክርስቲያን ማለት ስለ ኀጢአት አጣብቂኝ ኢየሱስ ክርስቶስ መፍትሔ እንደሆነ የሚያምን እና ለዳግም ልደት ጥያቄ የሚያቀርብ ነው።

## ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነው።

አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች የተባሉት በአንጾኪያ ከተማ ነበር። አንጾኪያ ትልቅ ከተማ ነበረች። በግምት 300,000

Free digital copy from ServeNow

ሕዝብ ይኖርበት ነበር። ጥቂቶቹ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የተለየ ኑሮ ይኖሩ ስለ ነበረ የአንጾኪያ ሰዎች ክርስቲያኖች እነዚህን አማኞች ክርስቲያኖች ብለው ሰየሟቸው።

ልዩ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምንድነው? ካለፈው አሮጌ ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ ወደሚገኘው አዲሱ ሕይወት ያመጣቸው የእግዚአብሔር ጸጋ ሲሆን ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት እና በመጨረሻም የሥጋ ትንሣኤው በኩል ነው። የሰው ልጅ ድኅነትን በሥራ አያገኘውም። ነገር ግን በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው።

## ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ደቀ መዝሙር ማለት ከመምህሩ የሚማር እና ዕለት ዕለት ከርሱ ጋ የሚጓዝ ሰው ነበር።

ዛሬ ግን ኢየሱስን በቃሉ እና በጸሎት በኩል መስማት ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን የርሱ ተከታይ መሆን እንችላለን።

## ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ይገልጻል። እግዚአብሔር ያድርበት ዘንድ ቤተ መቅደስ እንዲሠሩለት አይሁዳዊያንን እንደጠየቃቸው እኛም ክርስቲያኖች በመንፈሱ ልንሞላ ወይም መንፈሱ ልባችንን እና አእምሮአችንን እንዲሞላብን መፍቀድ ያለብን ሲሆን ይህም ያለንን አቅም እና ችሎታዎችን ለእግዚአብሔር ክብር ቅድሚያ በመስጠት ነው።

## ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቃል።

ክርስቲያን መሆናችን በምድር በሕይወት እስካለን ጊዜ ብቻ አይደለም። ለዘለአለም የእግዚአብሔር ስለሆንን አዲሱን

Free digital copy from ServeNow

ሕይወታችንን በመንግሥቱ በትንሣኤው በተለወጠው ሰውነታችን ከርሱ ጋር ለማሳለፍ እንጠባበቃለን።

## ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን አዘውትሮ ያነባል።

በየትኛውም የዓለም ክፍል ብትሄድ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡና የሚያጠኑ ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸው። ለምን?

### *መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢየሱስ ይጠቁመናል*

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች ውስጥ ምንም አስማት የለም። የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ወደ ሕያው ቃል (ኢየሱስ) እየጠቆመን "ወደ ኢየሱስ ሂድ" ይለናል። ወደ ኢየሱስ ካልሄድን መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ዐቢይ ዓላማ እንስታለን።

### *ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ ምንጭ ነው።*

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ሊሄዱበት በተገባ መንገድ ላይ እንደሚያበራ መብራት ነው። ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ኢየሱስ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሊያዉቋቸው የሚገባቸው ነገሮች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። ከእግዚአብሔር ጋራ ስላለህ ኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ምንጭ ነው። የሕሊናህ መሪ ይሆናል።

### *መጽሐፍ ቅዱስ ከሰይጣን ጋር ላለህ ውጊያ ያስታጥቅሃል።*

ኢየሱስ በሰይጣን በምድረ በዳ በተፈተነ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅስ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል አብዝተን ባወቅን መጠን ለመንፈሳዊ አቅም ዓይነተኛ መሣሪያ ይሆንልናል። የትኛውንም ፈተና የማሸነፊያ ሰይፋችን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

### *መጽሐፍ ቅዱስ ለማገልገል የኃይል ምንጫችን ነው።*

እንደ ክርስቲያን ይህችን ዓለም ለማገልገል ተጠርተሃል፣ በዙሪያህ ያሉትን ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመጡ

Free digital copy from ServeNow

እና ተከታዮቹ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ማገልገል በአካላዊ እና ስሜታዊ ፍላጎት ውስጥ ላሉት መራራትን ያካትታል።

***መጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳተ አኗኗርን ያስተካክላል።***

*ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ* (2 ጢሞቴዎስ 3:16)።

***መጽሐፍ ቅዱስ ማስተዋልን ያዳብራል።***

መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያን እንደ ምግብ ሆኖ ደግሞም የተለየ ነው። ለአካላዊ ፍላጎትህ የሚያስፈልግህን ያክል በበላህ ቁጥር ትጠግባለህ። ሆኖም ግን መንፈሳዊ ምግብን አብዝተህ ስትበላ የበለጠ የእግዚአብሔር ነገር ራብ ይኖርሃል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ያለህን መረዳት ያዳብራል፣ ስለርሱ አብዝተህ እንድታውቅ ፍላጎት ያሳድርብሃል ደግሞም ወደ ርሱ እንድትጠጋ ያደርግሃል።

## ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለው።

***ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ተግባቦት አለው።***

ጸሎት በግለሰብ ላይ የሚያጠነጥን ሥርዓት አይደለም። እንደ ክርስቲያን ስትጸልይ ተተኳሪው አካል እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ለወዳጆቹ በሰማይ ካለው አባታቸው ጋራ እንዲነጋገሩ እና ትርጉም የለሽ የቃላት ድግግሞሽ እንዲያስወግዱ ያስተምር ነበር። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋራ ኅብረት እንዲኖረን ያደርጋል። ይህንንም ከኢየሱስ ምሳሌ ልንማር ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ ለብቻው ከደቀመዛሙርት ተለይቶ በመሄድ የጸሎት ጊዜውን ከአባቱ ጋ ያሳልፍ ነበር።

***ክርስቲያን በጸሎት በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያድጋል።***

ጸሎት ልክ እንደ መተንፈስ ነው፤ ደግሞም የክርስቲያን ሕይወት ነው። ዘወትር ስንጸልይ ዘወትር በባሕሪአችን እና

Free digital copy from ServeNow

በውስጥ ማንነታችን በእድገት ላይ እንሆናለን። ጸሎት የደካማነት ሳይሆን የጥንካሬ እና የለውጥ ምልክት ነው። ጸሎት እንደ ትምህርት ነው። ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እንዲያስተምራቸው ፈልገው ስለ ነበረ ኢየሱስ ቤት ክርስቲያን ፈጽሞ መርሳት የማይገባትን የጸሎት ሥርዓት አስተማራቸው። በየዘመናቱ የነበሩ ክርስቲያኖች ይህንኑ ትምህርት፣ ሥርዓት እና በእግዚአብሔር የማደግ መብቶችን አግኝተዋል።

## ***ክርስቲያን በጸሎት እግዚአብሔርን ያወድሳል።***

የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ በመሆናችን እግዚአብሔርን በሁሉ ነገር ማክበር ይጠበቅብናል። በአዱስ ኪዳን ምሥጋና፣ ሐሤት ማድረግ እና ውዳሴ ቁልፍ የሆኑ የክርስቲያን ባሕሪአት ናቸው። የዳዊት መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት እና ለሕዝቡ ስላደረገው ነገር ደጋግሞ ያስተምረናል። የእግዚአብሔርን ባሕሪአት – ተፈጥሮአዊ ማንነቱን እና አፍቃሪነቱን ስናሰላስል፣ ውዳሴ ወሳኝ የጸሎታችን አካል ይሆናል።

## ***ክርስቲያን በጸሎት እግዚአብሔርን ያመሰግናል።***

*ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ* (ኤፌሶን 5:20)። አብዛኞቻችን አንዳንዴ በተለያዩ ጉዳዮች ሰበብ ምስጋና እናቀርባለን። በመንፈስ የተሞሉ አማኞች ደግሞ ዘወትር ስለ ሁሉም ነገር ያመሰግናሉ። ይህንንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያደርጋሉ።

## ***ክርስቲያን በጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይለማመዳል።***

ጸሎት ፈቃዳችንን በእግዚአብሔር ላይ የምንጭንበት ሳይሆን እግዚአብሔር ለኛ ካለው ፈቃድ ጋር የምናገኝበት ነው። በጸሎት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንገናኛለን። ለእግዚአብሔር

Free digital copy from ServeNow

ፈቃድ መገዛት እና እራሳችንንም ከርሱ ጋር ማገናኘት አለብን። እያንዳንዱ እውነተኛ ጸሎት "ፈቃድህ ይሁን" በሚል ፍሬ አሳብ ላይ ያጠነጠነ መሆን ይኖርበታል። ይህም መምህራችን ያስተማረን እና የሰጠን ሥርዓት ነው። ከመስቀል በፊት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን የማለትን ታላቅ ምሳሌ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ በጸለየበት ጊዜ ሰጥቶናል። *"አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን፡" አለ* (ማቴዎስ 26:39)።

## *ክርስቲያን በጸሎት ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ይገባል።*

የድል ጸሎት አንድን ክርስቲያን ወደ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ይወስዳል። ኤፌሶን 6፥18 ላይ እንዲህ ያለ ቃል እናገኛለን፦ *በጸሎትና በልመናም ሁሉ* **ዘወትር** *በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ።* ጸሎት ባለ ብዙ ዓይነት እና ቅርጽ ስለሆነ ዘወትር ያለማቋረጥ ደግሞም ያለ ተስፋ መቁረጥ ልክ እንደ ወታደር ንቁ በመሆን ለራስ እና ለቅዱሳን በሙሉ ወደ ጌታ መጸለይ የኅብረት እና አንድነት ማሳያም ነው። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ለተወሰኑት የእግዚአብሔር ሰዎች አልፎ አልፎ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በተወሰነ ጽናት ይጸልያሉ። ነገር ግን የተወሰነ የሚለውን ሁሉ በሚል ቃል በመተካት መጸለይ የጸሎታችንን አቅጣጫ በመልካም ይቀይራል።

## ክርስቲያን ስለ እምነቱ/ቷ ለሌሎች ያጋራል/ታጋራለች።

### *... ለሌሎች ስለ ክርስቶስ በማዉራት፣ ምክንያቱም*

ክርስትና ስለ ፍልስፍና ወይም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ ያተኮረ መሆኑን የቀደሙት ደቀ መዛሙርት ስለ ርሱ ማውራትን አድካሚ ወይም አሰልቺ ነገር አለመሆኑን አሳይተውናል። አንዳንዶቹ ደቀ መዛሙርት ተራ ነጋዴዎች፣ ሌሎቹም ምሁራን እና አብዛኞቹ ደግሞ ሴቶች ቢሆኑም ሁላቸውም ሕይወት ቀያሪውን የኢየሱስ

Free digital copy from ServeNow

ክርስቶስን ኃይል የተለማመዱ ናቸው። ይህም ኢየሱስን በቀላሉ ለሌሎች ማወጅ እንዲችሉ አድርጓቸዋል።

ሐዋሪያው ፊሊጶስ በጋዛ በረሃ በኩል ሲያቋርጥ ስለ ኢየሱስ ለኢትዮጵያዊው ጀንደረባ አውርቷል። ስለ ፊሊጶስ በሐዋርያት ሥራ 8፡ 26-40 ማንበብ ትችላላችሁ። ሁላችንም ከምናገኛቸው ከየትኞቹም ዓይነት ሰዎች ጋር ይህንኑ ርዕሰ ጉዳይ ማውራት እንችላለን። እያንዳንዳችን የኢየሱስ ምስክሮች እንድንሆን እንደተጠራን እንዲሁ ልንኖር የግድ ነው።

## *... እውነትን ለመግለጽ በመሞከር*

*ኢየሱስም አለው፡- "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም* (ዮሐንስ 14:6)።

ወደ ክርስቶስ በመምጣት መንገዱን ስታገኝ፣ ሕይወትን እንደማግኘት ዓይነት ልዩ ልምድ ይሆንሃል። ከዚያም ኢየሱስን ስትከተል፣ ስለ ርሱ ያሉትን እውነቶች በሙሉ በቻልከው መጠን ልትማር ያስፈልጋል። ይህም ደግሞ እውነቱን ለሌሎች ለማጋራት ያግዛል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር *መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰዓት ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና* (ሉቃስ 12:12)።

## *... ፍቅሩን በማጋራት*

ኢየሱስ ሲጠራን እና ወደ ዓለም ሁሉ ሲልከን ስለ ርሱ ከማውራት ላለፈ የሕይወት ዘይቤ ስለፈለገን ነው። እኛ የተለወጥንበትን የእግዚአብሔርን ፍቅር ዕለት ዕለት እንድንገልጠው ይሻል።

ኢየሱስ ከመያዙ እና ከመሰቀሉ አስቀድሞ ተከታዮቹን እንዲህ ብሏቸው ነበር፡- *ርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ ርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ* (ዮሐንስ 13:34)።

Free digital copy from ServeNow

### *... የተደረገልንን በመናገር*

ስለ ክርስቶስ ማውራት እንድናደርግ የምንገደድ ጉዳይ አይደለም። ከተደረገልን ነገር አንጻር እንድናደርገው ውስጣችን የሚገፋፋን ጉዳይ ነው። ስለ ራስህ ከክርስቶስ በፊት የነበረህን እና አሁን በክርስቶስ ከሆንህ በኋላ ያገኘኸውን የሕይወት ለውጥ አውራ። *እርሱም መለሰ፡- "ኀጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደ ነበርሁ፥ አሁንም እንዳይ፥ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ፥" አለ* (ዮሐንስ 9:25)።

## ክርስቲያን እና ዓለም

### *ክርስቲያን ከዓለም ውስጥ የተጠራ ነው።*

ክርስቲያን በዓለም የተከበበ ቢሆንም ከተከበብንባት ከዓለም ውስጥ ደግሞ የተጠራን ነን። የክርስቶስ የሆኑት ሰዎች በዓለም እንዳሉ ሰዎች ሊያስቡ ወይም ሊመላለሱ አይገባም፣ ይልቁንም ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ በክርስቶስ ዓይነት ልብ እና አሳብ ሊኖሩ ተጠርተዋል። ይህንንም አንዳንዴ ቅዱስ አኗኗር ብለን ስንጠራው በሌላ መልኩ መለየት ይባላል። የተቀደሰ ሰው የተለየ ሰው ነው። ጳውሎስ ለመጀመሪያዎቹ የሮሜ አማኞች ለማበረታታት ሲጽፍ፡-

*እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ* (ሮሜ 12:1-2:)።

Free digital copy from ServeNow

***ክርስቲያን ወደ ዓለም የተላከ ነው።***

ክርስቲያን በዓለማዊ ነገር ሊመረዝ ደግሞም ራሱንም ሸሽጎ ሊኖር የተገባው አይደለም። ነገር ግን ለዓለም ጨው እና ብርሃን ሊሆን እንደተጠራ ሰው ንጽህ እና አዎንታዊ ሕይወት እንዲኖረው ይጠበቃል።

***ክርስቲያን ዓለምን ድል የነሣ ነው።***

ይህ ከፍተኛ መጠን ያለው ጦርነት ነው። የዚህ ዓለም ክፉ ኃይላት ሊያጠምዱን እና ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን እንኖር ወደ ነበረው ሕይወት ወደ ኋላ ሊጎትቱን ይፈልጋሉ።

ከመጻሕቱ በአንደኛው፣ ሐዋሪያው ዮሐንስ ለሁሉ ሰዎች የሚሆን ምክሩን ሲጽፍ፡- *ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል* (1 ዮሐንስ 2:15-17) ይላል።

## ስለ ክርስቲያን ሕይወት የኢየሱስ ትምህርት

በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ኢየሱስ ስለ ሕይወት ብዙ ነገሮችን አስተምሮናል።

*ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፤ በተቀመጠም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው እንዲህም አለ፡-* (ማቴዎስ 5:1-2)።

በአጠቃላይ ይህንን የኢየሱስን ትምህርት ሥነ ብፁዓን ብለን እንጠራዋለን።

*በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።*

Free digital copy from ServeNow

*የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና። የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።*

*ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና። የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።*

*ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና። የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።*

*ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።*

*"ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና* (ማቴዎስ 5:3-12)።

በመቀጠልም፣ ኢየሱስ የምድር ጨው እና ብርሃን እንድንሆን አስተማረን፦

*"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።*

*"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ* (ማቴዎስ 5:13-16)።

## ***ኢየሱስ ስለ ሕግ አስተማረ።***

*"እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ*

Free digital copy from ServeNow

*ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።*

*እላችኋለሁና፦ ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም* (ማቴዎስ 5:17-20)።

## ኢየሱስ ስለ ቁጣ አስተማረ።

*"ለቀደሙት፦ 'አትግደል፥' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ 'የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል'። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም፦ 'ጨርቃም' የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ 'ደንቆሮ' የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።*

*"እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።*

*"አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ* (ማቴዎስ 5:21-25)።

## ኢየሱስ ስለ ዝሙት አስተማረ።

*"'አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል። ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። ቀኝ ዓይንህም*

Free digital copy from ServeNow

*ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና።*

*ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና*(ማቴዎስ 5:21-25)።

## ***ኢየሱስ ስለ ፍቺ አስተማረ።***

*'ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት፡' ተባለ። ፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል* (ማቴዎስ 5:31-32)።

## ***ኢየሱስ ስለ መሐላ አስተማረ።***

*"ደግሞ ለቀደሙት፡- 'በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ፡' እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡- ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል፥ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ 'አዎን አዎን' ወይም 'አይደለም አይደለም' ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው* (ማቴዎስ 5:33-37)።

## ***ኢየሱስ ቂም በቀል ስለ መያዝ አስተማረ።***

*'ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ፡' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን*

Free digital copy from ServeNow

*ከእርሱ ጋር ሂድ። ለሚለምንህ ስጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፈቀቅ አትበል* (ማቴዎስ 5:38-42)።

## ***ኢየሱስ ጠላቶችን ስለ መውደድ አስተማረ።***

*‘ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ፡’ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ* (ማቴዎስ 5:43-48)።

## ***ኢየሱስ ስለ ምጽዋት አሰጣጥ አስተማረ።***

*“ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። “እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል* (ማቴዎስ 6:1-4)።

## ***ኢየሱስ ስለ ጾም እና ጸሎት አስተማረ።***

*“ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም*

Free digital copy from ServeNow

*ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።*

*አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ። ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና። "እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፦*

*'በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤*

*መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤*

*የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥ በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉም አድነን እንጂ፥ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።'*

*"ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም። "ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል* (ማቴዎስ 6:5-18)።

## ***ኢየሱስ ስለ ገንዘብ እና ሃብት አስተማረ።***

*"ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና። "የሰውነት*

Free digital copy from ServeNow

*መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤*

*ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!*

*"ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።*

*ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?*

*"ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። "እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?*

*እንግዲህ፦ 'ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?' ብላችሁ አትጨነቁ፤ "ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።*

*ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል* (ማቴዎስ 6፡19-34)።

Free digital copy from ServeNow

## *ኢየሱስ በሌሎች ላይ መፍረድ የማይገባ መሆኑን አስተማረ።*

*"እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።*

*በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?ወይም ወንድምህን፦ 'ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ፡' እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፥ በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።*

*በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ* (ማቴዎስ 7:1-6)።

## *ኢየሱስ ስለ ውጤታማ ጸሎት አስተማረ።*

*"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።*

*ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው* (ማቴዎስ 7: 7-11)?

Free digital copy from ServeNow

## *ኢየሱስ ስለ ወርቃማው ሕግ አስተማረ።*

*እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና* (ማቴዎስ 7:12)።

## *ኢየሱስ ስለ ጠባቡ ደጅ አስተማረ።*

*"በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው* (ማቴዎስ 7:13-14)።

## *ኢየሱስ ዛፍ በፍሬው መታወቁን አስተማረ*

*"የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ* (ማቴዎስ 7:13-14)።

## *ኢየሱስ ስለ እውነተኞቹ ደቀ መዛሙርት አስተማረ።*

*በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፡- 'ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?' ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡- 'ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ፡ ' ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ* (ማቴዎስ 7:21-23)።

Free digital copy from ServeNow

### *ኢየሱስ በጠንካራ መሠረት ላይ ስለ ማነጽ አስተማረ።*

*“ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ* (ማቴዎስ 7:24-25)።

### *ኢየሱስ በሥልጣን አስተማረ።*

*ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤ እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና* (ማቴዎስ 7፡ 28-29)።

## ክርስቲያን የሆነን ሰው ወደፊት ምን ይጠብቀዋል?

የአንድ ግለሰብ ከክርስቶስ ጋር በመወዳጀት ክርስቲያን መሆን ልክ ትዳር ውስጥ እንደ መግባት ነው። ዳሩ ግን የኢየሱስ መሆንህን እንዴት እርግጠኛ መሆን ትችላለህ? ክርስቲያን መሆንህን እና በጠየቅኸው መሠረት መንፈሱ ወደ ሕይወትህ መምጣቱን እንዴት ማወቅ ትችላለህ?

### *የመጠራጠር ችግር*

ጥርጣሬ ሽባ ያደርግሃል። እንደ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹን ቀናት በጥርጣሬ መሞላት የተለመደ ነው። አንደንድ ጊዜ ከዚያ የውስጥ ማንነትህ የምትሰማው ድምጽ “አሁን አንተ ክርስቲያን ነህ? አስቂኝ ነህ” ወይም “በእርግጥ እግዚአብሔር ይቀበለኛል ብለህ ታስባለህ?” ይለናል። እንዴት ማወቅ ትችላለህ?

Free digital copy from ServeNow

## *የክርስቶስ ተስፋዎች*

መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወቱን ለክርስቶስ አሳልፎ በሰጠው ሰው ውስጥ በሚፈጸሙት ተስፋዎች የተሞላ ነው።

ሕይወትህን ለክርስቶስ አሳልፈህ ስትሰጥ ባንተ መሆን ስለሚጀምሩት ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቃል ኪዳናት የተሞላ ነው። *ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም*(ዮሐንስ 6:37)። *እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ* (ማቴዎስ 11:28)።

*እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል* (የዮሐንስ ራእይ 3:20)።

ምናልባት አደርጋለሁ ሳይሆን ሊያደርግ የሚችለውን ሁሉ ተናገረ። ይህ ተስፋ ነው።

*እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም* (ዮሐንስ 5:24)።

በ1 ዮሐንስ 5:11-13 *እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።* የሚል እግዚአብሔር ያጸደቀውን የተስፋ ቃል እናነባለን።

## *የክርስቲያን ሕይወት ቀለል ያለ ነው?*

ኢየሱስ የመጣው የዘላለምን ሕይወት ሊሰጠን ብቻ ሳይሆን የምድር ሕይወታችንም አሁን እንዲባዛልን ነው። ይህም የክርስቲያንን ሕይወት ሁል ጊዜ ቀላል ያደርጋል ማለት አይደለም። ኢየሱስ እንዲህ አለን፣ *በዓለም ሳላችሁ መከራ*

Free digital copy from ServeNow

*አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ* (ዮሐንስ 16:33)።

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞች ዕለት ዕለት ስለ እምነታቸው ቢሰደዱም ከክፉ ሁሉ ግን ይጠበቁ ነበር። ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በላይ በክርስቲያኖች ላይ ፈርጀ ብዙ ስደት ይደርስባቸዋል። ክርስቲያን መሆን ቀላል ባይሆንም የኋላ ኋላ ታላቅ ዋጋ አለው።

## ለአሸናፊ ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚሆን እርዳታ

እንደ ክርስቲያን መኖር በውስን ሰው ሰራሽ ሕግጋት፣ ባሕሎች እና ገደቦች ላይ የተመሠረተ አይደለም። በአንጽሩ የክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ዕለት ዕለት በቁርጠኝነት የምንኖረው ሕይወታችንን ለለወጠው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ *ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ* (ዮሐንስ 14:21)።

- የእግዚአብሔርን ቃል አንብብ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለእኛ ለአማኞች ያለውን ተስፋ ልብ በል። ተስፋዎቹ የነፍሳችን ምግቦች ናቸው። *በድኅነታችሁ እንድታድጉ፣ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ*(1 ጴጥሮስ 2፥2)። ልትራመድበት በተገባህ መንግድ ሁሉ ላይ ብርሃንህ ነው። *ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው* (መዝሙር 119:105)።
- በጌታ በኢየሱስ ስም ወደ ሰማያዊው አባትህ ዘወትር ጸልይ። *ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ* (ኤፌሶን 5:20)።
- ስለ በረከቱ እያመሰገንህ በሕይወትህ ሊያጋጥምህ ስለሚችል ኅጢአት እና ድካም ሁሉ ላይ ድልን እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ጠይቅ። *በኅጢአታችን ብንናዘዝ ኅጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ*

Free digital copy from ServeNow

*ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው* (1 ዮሐንስ 1:9)። ሌሎች ሰዎች ስለሚያስፈልጋቸው ነገሮችም ጸልይ። ዘወትር ስትጸልይ መንፈሳዊ ጥንካሬህ እየጎለበተ ደግሞም እየጨመረ ይሄዳል።

- ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ እና ወዳጅ አድርገህ ለሌሎች ተናገር። (ሮሜ 10፡ 9-10)። በዙሪያህ በጥፋት ውስጥ ለሚገኙ ሁሉ የክርስቶስ እንደራሴ ትሆናለህ (2 ቆሮንቶስ 5፡ 17-21)።
- ፈተና ከሚሆኑብህ ሁሉ በተቻለ መጠን እራስህን አርቅ። ሁሌም ፈተና ይኖራል፣ ነገር ግን መንገዳችንን ጠንቅቀን መምረጥ አስፈላጊ ነው። ደግሞም ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ላይ የሚያጠሉትንም ሆነ የሚያንገዳግዱትን ሁሉ ለማራቅ መሞከር ተገቢ ነው። *ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ* (1 ተሰሎንቄ 5:22)።
- እግዚአብሔርን በደስታ አገልግል። *በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ* (መዝሙር 100:2)። እንድታገለግለው እግዚአብሔር ላንተም ሥፍራ አለው።
- አእምሮህ በመታደስ ይለወጥ። *የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ* (ሮሜ 12:2)።
- ከክርስቶስ ተከታዮች *ጋራ* ኅብረት አድርግ። የአማኞች ኅብረትን ተቀላቀል። አብረኻቸው አምልክ፣ ጸልይ፣ አገልጋዮችም እንዲያገለግሉህ ፍቀድ። ጊዜህን፣ ገንዘብህን እና ተሰጥዖህን ሁሉ ለዘላለማዊ ጉዳይ እንዲውሉ አድርጋቸው።
- ልብህ በላይ ካለው ነገር *ጋራ* ይቆራኝ። *እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። ሞታችኋልና፥*

Free digital copy from ServeNow

*ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና* (ቆላስይስ 3: 1-3)።

- የክርስቶስ ፍቅር ይሙላብህ። *ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ* (ፊልጵስዩስ 2: 3-4)።
- ከሁሉ በላይ ግን ፍቅር ይኑርህ። *በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል* (1 ቆሮንቶስ 13:1-7)።

*አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ፡ ’ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም፦ ‘ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፡ ’ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም* (ማርቆስ 12: 30-31)።

Free digital copy from ServeNow

## ለጥናት እና ግብረ መልስ የሚሆኑ ጥያቄዎች

- ክርስቲያን ማን ነው የሚል አያሌ ጥያቄዎች አሉ። አንተ የትኛውን ታምናለህ?
- ስለ ክርስትና መሠረታዊ እምነትህ ምንድነው?
- የክርስቲያን ባሕርያት ከሚባሉት መካከል ጥቂቶችን ዘርዝር።
- ከነዚህስ የትኞቹን ለማሻሻል ትሞክራለህ?
- እነዚህን እንዴት እየተገበርካቸው ነው?
- የክርስቲያን በዓለም ውስጥ መኖር እና ከዓለም አለመሆን ምን ማለት ነው?
- ኢየሱስ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን አስተምሯል። ጥቂቶቹን ከነማብራሪያቸው በመጥቀስ ላንተ ያላቸውን ጠቀሜታ መዘረዘር ትችላለህ?
- የክርስትና ሕይወትን እንዴት እንድንኖር ይጠበቅብናል?
- የክርስትና ሕይወትህን ድምቀት እና ተጨባጭነት የሚያሳዩ ሁለት ወይም ሦስት መንገዶችን ጥቀስ።